# የጥገኝነት የመኖርያ ፍቃድ ለተሰጣቸው ሰዎች ከቤተሰባቸው ጋር በድጋሚ የማገናኘት ሂደት

**የጥገኝነት የመኖርያ ፍቃድ ኣለዎት ከቤተሰባችሁ ጋር በድጋሚ የማገናኘት ሂደት መጠየቕ ትፈልጋላቹ**

ግዝያዊ የመኖርያ ፍቃድ የተሰጥዎት ነዎት። እና አሁን የቤተሰብዎ አባላት ከውጭ አገር ወደ ኔዘርላንድ እንዲመጡ ይፈልጋሉ። እርስዎ ስፖንሰር ናችሁ.። ይህ ማለት እርስዎ የቤተሰብዎን አባላት ወክለው ማመልከቻ ያስገቡት ማለት ነው። የማመልከቻው ዓላማ የኔዘርላንድ የጥገኝነት ፍቃድ እንዲሰጥ ነው። ለዚህ መተግበሪያ ምንም ክፍያ ኣታደርጉም በነጻ ነው።

ቤተሰብን መልሶ የማገናኘት ሂደት ሁለት ክፍሎች አሉት፥

- ክፍል 1 ማመልከቻ ለውክልና ስልጣን ለግዝያዊ መኖርያ ፍቃድ (mvv) ክእርሶ ቦሃላ ወደዚህ ለሚመጡ የቤተሰብዎ አባላት የተመለከተ ነው። mvv ቪዛ ሆኖ ለረጅም ግዜ ልትኖርበት የምትችል ነው። የቤተሰብዎ አባላት ይህንን ቪዛ ተጠቅመው ወደ ኔዘርላንድ መግባት ይችላሉ።

- ክፍል 2 የቤተሰብዎ አባላት ወደ ኔዘርላንድ ከመጡ በኋላ የጥገኝነት ፈቃድን መስጠት የተመለከተ ነው። የቤተሰብዎ አባላት በርስዎ የጥገኝነት ፍቃድ ላይ የተመሠረተ የመኖርያ ፍቃድ ያገኛሉ። የቤተሰብዎ አባላት የመቆየት ሁኔታ እርስዎ ካሉት የጥገኝነት ፍቃድ የተመሠረተ እና የተያያዘ ነው።

በዚህ ወረቀት ውስጥ የቤተሰብዎ አባል እንዴት በርስዎ የጥገኝነት ፍቃድ ላይ የተመሠረተ የመኖርያ ፍቃድ ማግኘት እንደሚችሉ ደረጃ በደረጃ ማንበብ ይችላሉ።

# በሌላ ሰው የጥገኝነት ፍቃድ ላይ የተመሠረተ የጥገኝነት ፍቃድ፥ የቤተሰብ አባላት እና ቅድመ ሁኔታዎች

በሌላ ሰው የጥገኝነት ፍቃድ ላይ የተመሠረተ የጥገኝነት ፍቃድ የቤተሰብዎ አባላት በኔዘርላንድ ውስጥ ከእርስዎ ጋር አብሮ ለመኖር የሚያስችል ህጋዊ ፈቃድ ነው። ይህን ፍቃድ ለማግኘት እርስዎ እና የቤተሰብ አባሎችዎ በስደተኞች ህግ ውስጥ ያሉትን ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላት አለብዎት።

## በሌላ ሰው የጥገኝነት ፍቃድ ላይ የተመሠረተ የጥገኝነት ፍቃድ ለማግኘት የሚችሉ የቤተሰብ አባላት

1. በህጋዊ ጋብቻ የተጋቡት ወይም በተመሳሳይ ሁኔታ የተዛመዱት፣
2. ከእድሜ በታች የሆኔ ልጅዎ ወይም የባለቤትዎ ልጅ የቤተሰብዎ አባል የሆነ። ይህ ለበተፈጥሮ ከዘርዎ (ባዮሎጂካል) ለወለዱት ወይም እንደ ሞግዚት ሆነው ላሳደጉት ልጅዎ ጭምር ይሰራል።
3. ከቤተሰብዎ ውስጥ የሆነ ለአካለ መጠን የደረሰው ልጅዎ። ከልጅዎ ጋር ያለው የቤተሰብ ግንኙነት ገና ቀጣይ የሆነ። ይህ ለበተፈጥሮ ከዘርዎ (ባዮሎጂካል) ለወለዱት ወይም እንደ ሞግዚት ሆነው ላሳደጉት ልጅዎ ጭምር ይሰራልል። ከ 25 ዓመት በላይ ለሆኑ ልጅዎ፣ ከመጠን ባለፈ የሌላ ሰው ጥገኛ መሆን አለበት።
4. የተፈጥሮ (ባዮሎጂካል) በዘራቸው የወለዷቻው የወላጅ አባት ወይም እናት፣ ዕድሜዎ ከተገቢ ዕድሜ በታች ከሆነ እና ያልተጋቡ ከሆኑ።

## ቅድመ ሁኔታዎች ለ በሌላ ሰው የጥገኝነት ፍቃድ ላይ የተመሠረተ የጥገኝነት ፍቃድን ለማግኘት

- የቤተሰብዎ አባሎች በተሰጣቸው ቀነ ገደብ ውስጥ ወደ ኔዘርላንድ መግባት አለባቸው። ቀነ ገደብ ስንል በ 3 ወራት ጊዜ ውስጥ ነው። ይህ የድሕረ ጉዞ ቀነ ገደብ ነው። የድሕረ ጉዞ ቀነ ገደብ የሚጀምረው ጥገኝነት ፈቃድ ካገኙበት ቀን በኋላ ጀምሮ ነው። የቤተሰብ አባሎችዎ በሁለት መንገዶች ወደ ኔዘርላንድ ሊገቡ ይችላሉ።
  1. የቤተሰብዎ አባሎች ልክ በተመደበላቸው ቀነ ገደብ ወይም ከዚያ ቀደም ብለው ወደ ኔዘርላንድን ይገባሉ።
  2. የቤተሰብዎ አባሎች በተመደበላቸው የድሕረ ጉዞ ቀነ ገደብ ውስጥ በርስዎ በኩል የጥገኝነት ማመልከቻ ለ ቆይተው ለሚጓዙ mvv ይጠይቃሉ።
- የቤተሰብዎ አባላት ድሮም እዛ ውጭ ኣገር የቤተሰብዎ አባል የነበሩ መሆን ኣለባቸው። ይህም የቤተሰብ ትስስር ተብሎ ይጠራል። የቤተሰብ አባሎችዎ ወደ ኔዘርላንድ ከገቡ ቦኋላም ቤተሰባዊ ግንኙነት ገና መኖር ኣለበት።
- የቤተሰብዎ አባላት ማንነታቸው ኣና ከእርሶ ጋር ያላቸው ዝምድና ለማሳየት ሰነዶቻቸውን በማቅረብ ማረጋገጥ ኣለባቸው። ከዚህ በታች ስለ ሰነዶች በበለጠ ማንበብ ትችላላችሁ።
- ከ 12 ዓመት በላይ የሆኑት የቤተሰብዎ አባላት በማመልከቻው ወንጀለኛ አለመሆናቸውን የሚገልጽ የምስክር ወረቀት መፈረም አለባቸው። ይህ (antecedentenverklaring) ይባላል።
- ከማመልከቻው ጋር እድሜያቸው 15 እና ከዚያ በላይ የሆኑ ቤተሰቦችዎ የጋብቻ ሁኔታ ማረጋገጫ ወረቀት መፈረም አለባቸው።
- በሌላ ሰው የጥገኝነት ፍቃድ ላይ ያልተመሰረተ የራስዎ የግልዎ ራሱን የቻለ የጥገኝነት ፍቃድ ያገኛችሁ መሆን ኣለባቹሁ።
- የቤተሰብዎ አባላት ወኪል መሆናቹን የሚገልጽ የምስክር ወረቀት መፈረም አለባቹሁ።.
- በጥገኝነት ጥያቄ ሂደት ወቅት የቤተሰብዎን አባላት ያስመዘገቡ መሆን ኣለባቹሁ።
- እርሶ እና ባለቤትዎ 18 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ናቸው።
- ከተገቢ ዕድሜ በታች ለሆነው ልጅዎ ማመልከቻ የሚያቀርቡ ከሆኑ እና የልጁ ሌላኛው ሁለተኛው ወላጅ በውጭ አገር የሚኖር ከሆነ፣ ይህ ሌላኛው ወላጅ ልጅዎን ወደ ኔዘርላንድ ለመሄድ ፍቃድ መስጠት አለበት።

ከአንድ በላይ ያገቡት ባለቤት አለዎት? እንደዛ ከሆነ ኣንድ ባለቤት እና ከዛ ባለቤት ጋር ኣብረው የወለድዋቸውን ልጆች ብቻ ናቸው ወደ ኔዘርላንድ ማስመጣት የምትችሉ። እንደ የኔዘርላንድ ሕግ አንድ ዜጋ ሊኖረው የሚፈቀድ አንድ ጋብቻ ብቻ ነው።

## ለበሌላ ሰው የጥገኝነት ፍቃድ ላይ የተመሠረተ የጥገኝነት ፍቃድ የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎችን አያሟሉም

በሚከተሉት ሁኔታዎች የቤተሰብዎ አባላት እና እርስዎ መሟላት ያለባቸውን ቅድመ ሁኔታዎች አያሟሉም፥

- የድሕረ ጉዞ ቀነ ገደብ አልፏል። IND ምህረት መስጠት ያለበት ከሆነ ያመዛዝናል።
- እዚህ ከተጠቀሱት የቤተሰብ አባላት ውጭ ሌላ ኣይነት የቤተሰብ ኣባል ማስመጣት ከፈለጋችሁ።
- እርስዎ ራስዎ ያገኙትን የጥገኝነት ፍቃድ በሌላ ሰው የጥገኝነት ፍቃድ ላይ የተመሠረተ ነው።

በእነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ ለቤተሰብ መልሶ ማገናኘት ማመልከቻ ማቅረብ ይፈልጋሉ? ኣንደዛ ከሆነ የተለመዱትን የማመልከቻዎች ሂደቶች መከተል አለብዎት። እነኝህን ሂደቶችን ለማካሄድ የገንዘብ ክፍያ ማድረግ ያስፈልጋል። በተጨማሪ ደሞ ህጎቹ በጣም ከባድ ናቸው። ይህን ለማድረግ ‘Aanvraag voor het verblijfsdoel familie en gezin (referent)’ የሚል ቅጽ (ፎርም) ተጠቀሙ። ይህን ቅጽ (ፎርም) ወደ www.ind.nl/familie. የሚል የኢንተርነት ድህረ ገጽ በመሄድ ማግኘት ይችላሉ።

## እርስዎ ከተገቢ ዕድሜ በታች ኣና ለብቻቹ የምትኖሩ የቤተሰብዎ አባሎች ተጠሪ (ስፖንሰር አድራጊ) ናችሁ

በዚህ ሁኔታ፣ የቤተሰብ መልሶ ማገናኘት ማመልከቻ ለበተፈጥሮ (ባዩሎጂካል) የወለድዎት ለወላጆችዎ ብቻ ማቅረብ ይችላሉ።

ከተገቢ ዕድሜ በታች ለሆኑ እና ለአዋቂዎች እህት እና ወንድሞቻችሁ ማስመጣት ከፈለጋችሁ የተለመዱትን የማመልከቻዎች ሂደቶች መከተል አለብዎት። ይህን ለማድረግ ‘Aanvraag voor het verblijfsdoel familie en gezin’ የሚል ቅጽ (ፎርም) ተጠቀሙ። እነኝህ ሂደቶችን ለማካሄድ ገንዘብ መክፈል ያስፈልጋል።

# ለቤተሰብዎ እና ለእርስዎ ሊያጋጥሚቸው የሚችሉ ድርጅቶች

Ministerie van Buitenlandse Zaken

**የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር** (BZ) በውጭ አገሮች የኔዘርላንድ መንግሥትን ይወክላል። BZ በዓለም ዙሪያ በተለያዩ ሀገራት ኤምባሲዎች አሉት። የኔዘርላንድ ኢምባሲዎች ለቤተሰብዎን የመልሶ ማገናኘት ማመልከቻዎን ለማቅረብ ለቤተሰብዎ ሊደግፉ ይችላሉ። ኤምባሲዎች ለቤተሰብዎ ቀጠሮ በመያዝ የ DNA ምርመራ እና ቃለ መጠይቅ ማካሄድ ይችላሉ። ይሄ ሁል ጊዜ IND ጥያቄ ስያቀርብ ነው የሚፈጸመው። IND የቤተሰብዎ አባላት mvv መሰጠት ኣለባቸው ብሎ ከወሰነ ከዚያ የቤተሰብዎ አባላት ወደ ኤምባሲው በመሄድ mvv እንዲሰጣቸው ማመልከቻ በማቅረብ ሂደቱን ይጀምራሉ። (www.rijksoverheid.nl)

Immigratie- en Naturalisatiedienst
*Ministerie van Justitie en Veiligheid*

**የኢሚግሬሽንና የዜግነት ጉዳይ** (IND) የኔዘርላንድ የፍትህ እና ደህንነት ሚኒስቴር አካል ነው። የ IND ሰራተኞች የቤተሰብዎን አባላት ለመልሶ ማገናኘት የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎችን ያሟሉ እንደሆነ ይመረምራሉ። ሁሉም የቀረቡት የሰነዶችን ትክክለኛነት ይመረምራሉ። በተጨማሪም በውጭ አገር የሚያስፈልጉ ተጨማሪ ምርመራ እና ጥናቶችን መጀመር ይችላሉ። እነኝህ ደግሞ የ DNA ምርመራ እና ከቤተሰብዎ አባላት ጋር ቃለ-ምልልስ ማካሄድ ናቸው። የ IND ሠራተኞች ለእርስዎም በኔዘርላንድ ኣንዳንድ ጥያቄዎች ሊጠይቁዎት ይችላሉ። ከዚያም የቤተሰቦቻችሁ አባላት ወደ ኔዘርላንድ መምጣት ይችላሉ ወይም መምጣት ኣይችሉም ብለው ይወስናሉ። (www.ind.nl)

gza healthcare

**የጥገኝነት ጠያቄዎች የጤና እንክብካቤ (GZA)** ህመም ካለብዎ ወይም የህክምና ጥያቄዎች ካለዎት የሚሄዱበት ድርጅት ነው። በእያንዳንዱ የ COA የስደተኞች መጠለያ ቦታ ውስጥ ወይም ደግሞ በእያንዳንዱ የ COA የስደተኞች መጠለያ ቦታ አጠገብ የ GZA የጤና ማዕከል ይገኛል። GZA ለእርስዎ ከ ዶክተር ረዳት, ነርስ, አጠቃላይ የህክምና ረዳት GGZ ወይም የግልዎ ሃኪም ቀጠሮዎችን ያካሂዳል። ለሕክምና ጥያቄዎች ወደ የሕክምና መቀበያ 'de Praktijklijn' በስልክ ቁጥር 088 112 21 12 ቀንም ሆነ ሌሊት መደወል ይችላሉ። ከሰኞ እስከ አርብ ባለው ግዜ ወደዚህ ቁጥር መደወል ይችላሉ። እንደዚሁም ለሕክምና ያልሆኑ ጥያቄዎች, ለምሳሌ ወደ ልዩ ባለሙያ (ስፔሽያሊስት) ማዘዋወር በተመለከተ።

VluchtelingenWerk
Nederland

**የኔዘርላንድ የስደተኞች ተባባሪዎች** (VWN) ከጥገኝነት ነጻ የሆነ የሰብአዊ መብት ተሚጋች ድርጅት ሲሆን, የጥገኝነት ጠያቂዎችንና ስደተኞችን ጥቅም የሚያስጠብቅ ነው። የ VWN ሰራተኞች ስለ የቤተሰብ መልሶ ማገናኘት ሂደት መረጃዎች ይሰጣሉ። የቤተሰብን መልሶ ማገናኘት ማመልከቻ ቅጽ ለሞምላት ሊረዱዎት ይችላሉ። በተጨማሪ ደግሞ ለእርስዎም ይሁን ለየቤተሰብዎ አባላት ለዚህ የቤተሰብ መልሶ ማገናኘት ሂደት በጠቅላላ ድጋፍ ይሰጧቹሃል። ከሌሎች ድርጅቶች ጋር ኣንዳንድ ችግሮች ሲገኙ ደግሞ እርዳታ ይሰጣሉ። VWN ስለ ቤተሰብ መልሶ ማገናኘት ማመልከቻዎች ምንም ውሳኔ መስጠት ኣይችልም።

COA Centraal Orgaan opvang asielzoekers

**ማዕከላዊ የጥገኝነት ጠያቂዎች ማቋቋምያ ኤጀንሲ** (COA) ስራው፣ በጥገኝነት አሠራሩ ሂደት ውስጥ የጥገኝነት ጠያቂዎችን ተቀብሎ መጠለያ እንድያገኙ ማድረግ እና መደጋገፍ ነው። ይህም ወደ ኔዘርላንድ ለመጓዝ ለተፈቀደላቸው የቤተሰብዎን አባላት ላይም ይመለከታል። COA አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የመኖርያ ቤት, ምግብ እና ጊዜያዊ የጤና መድን (ኢንሹራንስ) ይሰጣል። በመጠለያው ውስጥ ሐኪም ከፈለጉ COA ይረዳዎታል። COA ከጥገኝነት ነጻ የሆነ ድርጅት ሆኖ ስለ ቤተሰብ መልሶ ማገናኘት ማመልከቻዎች ምንም ውሳኔ መስጠት ኣይችልም። (www.coa.nl)

INTERNATIONAL ORGANIZATION FOR MIGRATION
IOM·OIM
THE UNITED NATIONS MIGRATION AGENCY

**የዓለም አቀፍ የስደተኞች ድርጅት** (IOM) በዓለም ዙሪያ ከሚገኙ ከ 100 በላይ በሚሆኑ አገሮች ውስጥ ከሚገኙት ጽህፈት ቤቶቹ ስደተኞችን ይደግፋል። ከድጋፎቹ ኣንዱ የጥገኝነት ፍቃድ ላገኙ ስደተኞች የቤተሰብ አባላትን ማዛወርን ነው። IOM ይህንን ለማድረግ የአገልግሎት ክፍያ ያስከፍላል። የሚያደርገው ትብብር ደግሞ ኣንዳንድ ድጋፍ በመስጠት ወይም የጉዞውን ሂደትን ሙሉ ሃላፍነት በመውሰድ ጠቅላላ የሆነ የጉዞ እርዳታ ማድረግ ነው። ለሁለቱም ዓይነት እርዳታዎች ኢንተርኔት በመጠቀም ዋጋን መጠየቅ አለብዎት። IOM ለቤተሰብ መልሶ ማገናኘት የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ ኣይችልም። (www.iom-nederland.nl)

# የጥገኝነት የመኖርያ ፍቃድ ለተሰጣችው ሰዎች ከቤተሰባቸው ጋር በድጋሚ የማገናኘት ሂደት



# ክፍል 1. የ mvv የጥገኝነት ማመልከቻ ቆይተው ለሚመጡ የቤተሰብ ኣባላት በ8 ደረጃዎች

## 1ኛ ደረጃ፥ ማመልከቻ ማስገባት

የማመልከቻ ቅጽ ሞልተው ያስገቡ። ይህ ቅጽ በ IND ድህረ ገጽ www.ind.nl/asiel ላይ ይገኛል (የስደተኛ የቤተሰብ አባል የሚል ይምረጡ)። ለእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል የተለየ ቅጽ መጠቀም አለብዎት። በ IND ድህረ ገጽ ላይ ሊጠቀሙበት የሚችሉ የእንግሊዝኛ ቅጽም አለ።
የ VWN ሰራተኞች ስለ ቤተሰብ መልሶ ማገናኘት አሰራር ሂደት መረጃ ይሰጣሉ። የማመልከቻ ቅጹን በመሙላት ደግሞ ሊረዱዎት ይችላሉ። በተጨማሪም ደግሞ ጠቅላላ የመልሶ ማገናኘት ሂደት ሊረዱዎት ይችላሉ። ዕድሜዎ ከተገቢ በታች ነው? የእርስዎ የ NIDOS አሳዳጊ በማመልከቻው ሂደት ሊረዱዎት ይችላሉ።

በማመልከቻ ቅጹ ላይ ያሉትን መመሪያዎች በሙሉ ያንብቡ እና ይከተሉ። ዝርዝር መረጃዎች ስለ የቤተሰብዎ አባላት ልክ እንደ በህጋዊ ሰነዶቻቸው ውስጥ እንደተመዘገቡት ኣድርገው ይምሉት። እነኝህ ደግሞ፣ ስም፣ የተወለዱበት ቀን፣የተወለዱበት ቦታ፣ ዜግነት እና የጋብቻ ሁኔታ ናቸው። ለእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ግልጽ እና ወቅታዊ የፓስፖርት ፎቶ መላክ ኣለብዎት። የጽሑፍ ጥያቄ በሚያቀርቡበት ግዜ የቤተሰብዎ የፓስፖርት ፎቶ ምንም ባልተጻፈበት የ (A4) ነጭ ወረቀት ላይ ይለጥፉት። ከፎቶው ጎን ደግማ የቤተሰብዎ የግል ዝርዝር መረጃዎች ይጻፉ።

IND ከቤተሰብዎ አባላት የሚጠብቀው ማንነታቸውን እና ከእርስዎ ጋር ያላቸው ቤተሰባዊ ግንኙነታቸውን ኦሪጂናል የሆኑት ሰነዶችን በማቅረብ እንዲያረጋግጡ ነው። እነዚህ ሰነዶች በትውልድ ሀገርዎ የመንግስት ባለስልጣናት የተሰጡ ህጋዊ (ኦፊሴላዊ) የሆኑ ሰነዶች ናቸው። ግን ደግሞ ኦፊሴላዊ ያልሆኑ ደጋፊ ሰነዶችም አሉ። ይህ ማለት ኣብዛኛው ግዜ እነኝህ ኦሪጂናል ሰነዶች የቤተሰብዎ አባላት ወደዚህ ወደ ኔዘርላንድ ለርስዎ መላክ አለባቸው ማለት ነው። IND የትኞቹ ህጋዊ ሰነዶች መላክ እንዳለባቸው ያመለክታል። እዚህ ላይ ለእራስዎ የሚያስፈልጉትን ሰነዶች ግምት ውስጥ ያስገባል። በአንድ ህጋዊ የሆነ መታወቂያ ሰነድ የልደት ቀን እና የልደት ቦታ የተጻፈበት እንዲሁም የፓስፖርት ፎቶ ያለበት መሆን አለበት።

ሁሉም የተጠየቁ ሰነዶች በሆላንድኛ, እንግሊዝኛ, ፈረንሳይኛ ወይም ጀርመንኛ የተጻፉ ወይም የተተረጎሙ መሆን አለባቸው። ተርጓሚው ደግሞ በሆላንድ ፍርድ ቤት ቀርቦ ቃለ መሐላ የፈጸመ መሆን አለበት።

> ለዚህ ማመልከቻ አስፈላጊ የሆኑትን ሁሉንም ሰነዶች በተቻለ መጠን በተሎ ይሰብስቡ። ይህ በማድረግ ሂደቱን ፈጣን እንዲሆን ታደርጋላችሁ።

### ሰነዶች

ሁሉም የትውልድ ሀገር ኣንድ ዓይነት የሆኑ ሰነዶችን የላቸውም። ስለዚህ ለእያንዳንድ ሀገር ለዚህ ሂደት ለመተግበሪያው የሚያስፈልጉትን ሰነዶች መዘርዘር ኣይቻልም። በጥቅል አነጋገር, IND የሚከተሉትን **የህግ ሰነዶች** ይቀበላል፥

- መታወቂያ: ፓስፖርት, የመታወቂያ ካርድ, የዜግነት ሰርተፊኬት ወይም የወታደር መፅሃፍ (ስም, የልደት ዝርዝሮች, የፓስፖርት ፎቶ የያዙ);
- የቤተሰብ ዝምድና: የጋብቻ የምስክር ወረቀት, የልደት የምስክር ወረቀት, የቤተሰብ ደብተር ወይም የቤተሰብ መዝገቦች ከሕዝብ መመዝገቢያ።

### ህጋዊ (ኦፊሴላዊ) ያልሆኑ ሰነዶችን የሚባሉት፥

- የትምህርት ቤት ካርድ, ዲፕሎማዎች, የክትባት ካርድ፡
- የመንደሩ አለቃ, ቤተክርስቲያን, መስጊድ, የሕግ ባለሙያ ወይም ባንክ የሚሰጡት ሰነዶች እና የምስክር ወረቀቶች፡
- የፎቶ ግራፍ ወይም ፊልም ሰነዶች።

ለእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል የሁሉም ሰነዶች ቅጂ እና የማመልከቻ ቅጽ ሞልተው ወደ IND መላክ አለብዎት። ከጊዜ በኋላ ሊያስፈልጉ ስለሚችሉ ህጋዊ (ኦሪጂናል) ሰነዶች በደንብ ማስቀመጥ አለብዎት።

ሙሉ በሙሉ የተሞላ የማመልከቻ ቅጽ እና ሁሉም ተያይዘው መላክ ያለባቸው ሰነዶች እንዲሁም የፓስፖርት ፎቶዎች ወደ IND ይላኩት። የ IND አድራሻ በማመልከቻ ቅጹ ላይ ተጽፎ ይገኛል።

## 2ኛ ደረጃ፥ ማመልከቻ መቀበልና መቆጣጠር

IND ማመልከቻውን ከተቀበለ ቦሃላ ከዚያ ለእርስዎ ደብዳቤ ይልክልዎታል። የደብዳቤው ይዞታ ደግሞ ማመልከቻውን ያስገቡለት የቤተሰብ አባል ስም፣ እንዲሁም IND ማመልከቻው የተቀበለበት ቀን እና መቼ ውሳኔ እንደሚሰጥ ያለበት ነው።

> ኣድራሻዎን ለመቀየር ኣስበዋል? ያልተፈለገ የሂደቱን መዘግየት ኣንዳይከሰት አዲሱ አድራሻዎን በተቻለ መጠን በተሎ ለ IND ያሳውቁ። ከየኔዘርላንድ የስደተኞች ተባባሪዎች VWN ኣዲስ ተባባሪ ከተደረገላቹሁ ደግሞ ይህንን መረጃ ለ IND ያሳውቁ። ለውጦችን ሲገኙ ሁል ግዜ ደብዳቤ በመላክ ያስተላልፉ።

ማመልከቻዎ ወደ IND ገብቶ በሂደት ላይ ከሆነ IND ማመልከቻውን ምንም ያልጎደለው የተሟላ እንደሆነ ይቆጣጠራል። ሁሉንም የተጠየቁ ዝርዝ መረጃዎች ሞልተው ያስስገቡ ከሆነ ማመልከቻው ተሟልቷል ለማለት ይቻላል። እንዲሁም ትክክለኛውን ሰነዶች እና ሌሎች የተጠየቁ ነገሮችን ካቀረቡ። ማመልከቻው የተሟላ ነው? ከዚያ IND የቤተሰብዎ ኣባላት በርስዎ የጥገኝነት ፍቃድ ላይ የተመሠረተ የመኖርያ ፍቃድ ለማግኘት የሚያስፈልጉትን ቅድመ ሁኔታዎች ያሟሉ እንደሆነ ይገመግማል። IND የቤተሰብዎ አባላት የሚያስፈልጉትን ሁኔታዎች ያላሟሉ መሆኑን በግልጽ ካወቀ ማመልከቻውን ውድቅ ያደርገዋል።

ማመልከቻው ያልተሟላ ነው? እንደዚያ ከሆነ ሂደቱ ብዙ ጊዜ ይወስዳል። ስለዚህ ጉዳይ በተመለከተ IND ደብዳቤ ይልክልዎታል። የደብዳቤው ይዘት ደግሞ ይህንን ማመልከቻ እንዴት የተሟላ ልታደርጉት እንደምትችሉ እና መቸ መተግበር እንዳለበት የሚገልጽ ነው። ደብዳቤውን በመያዝ በፍጥነት ወደ የ VWN ተባባሪዎ ይሂዱ። ተጨማሪ ጊዜ የሚያስፈልጎት ከሆነ ወደ የማመልከቻዎን ሂደት ለሚያካሂድ የ IND ሠራተኛ ደውለው ይንገሩ ወይም ደግሞ የ VWN ተባባሪዎ ይደውሉልዎት። የ IND ሰራተኛ ስልክ ቁጥር በደብዳቤው ውስጥ ተጽፎ ይገኛል።

## 3ኛ ደረጃ፥ የሰነዶች ምርመራ

ሁሉም የቤተሰብዎ አባላት ማንነታቸውን ሰነዶች መማቅረብ ማረጋገጥ አለባቸው። እንዲሁም በኔዘርላንድ ውስጥ ከእርስዎ ጋር ምን ዓይነት ዝምድና (ቤተሰባዊ ግንኙነት) ያላቸው እንደሆኑ ማረጋገጥ ኣለባቸው። ብዙውን ጊዜ የ IND ሰራተኞች እነዚህ ሰነዶች እውነተኛ መሆናቸውን ይመረምራሉ። IND ዋና (ኦሪጂናል) ሰነዶች ለመመርመር ከፈለገ ማብራሪያን የያዘ ደብዳቤ ይደርስዎታል። ይህ የሰነድ ምርመራ ለጥቂት ወራት ያህል ሊወስድ ይችላል።

የቤተሰብ አባላትዎ ኦፊሴላዊ ሰነዶች የላቸውም? እንደዛ ከሆነ IND የማስረጃ አስቸኳይ ሁኔታ አስፈላጊነት ካለ ይገመግማል። ይህ ማለት ደግሞ የእርስዎ የቤተሰብ አባል ከጥፋታቸው ውጪ ዶክመንቶችን ማቅረብ ኣልቻሉም ማለት ነው። ስለዚህ እርስዎ ለ IND የቤተሰብ አባላትዎ ለምን ህጋዊ (ኦፊሴላዊ) የሆኑ ሰነዶችን ማቅረብ እንዳልቻሉ በደንብ መግለፅ በጣም አስፈላጊ ነው። ነገር ግን የቤተሰብ አባላትዎ በሌሎች ህጋዊ ባልሆኑ ሰነዶች በማቅረብ ከእርስዎ ጋር ምን ዓይነት ዝምድና (ቤተሰባዊ ግንኙነት) ያላቸው እንደሆኑ ማረጋገጥ እንደሚቻል መግለፅ በጣም አስፈላጊ ነው።

## 4ኛ ደረጃ፥ የ DNA ምርመራ

አንዳንድ ጊዜ የቤተሰብዎ አባላት ያቀረቡት ሰነዶች በቂ አይደሉም። ወይም የቤተሰብዎ አባላት ሰነዶች የላቸውም። ከዚያ IND ለቤተሰብዎ አባላት የቀጣይ ምርመራ ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ። ይህ ሁኔታ የሚከሰተው IND የማስረጃ አስቸኳይ ሁኔታ ኣለ ብሎ ከገመገመ ነው።. DNA የቀጣይ ምርመራ ምሳሌ ነው። የቤተሰብዎ አባል ከዘርዎ የተገኘ ልጅዎ ነው? ወይም እርስዎ ከተገቢ ዕድሜ በታች ከሆኑ ወላጅዎ ከዘራቸው ያገኙዋቸው ናቸው? በዚህ ኣይነት ሁኔታ ከ IND ደብዳቤ ይደርስዎታል። ይህ ደብዳቤ ደግሞ IND የቤተሰብዎን አባላት የ DNA ምርመራ እንዲያደርጉ የሚጋብዝ ነው። በዚህ መንገድ ደግሞ የቤተሰብዎ አባላት ወላጅዎ ወይም ልጅዎ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይችላል። IND ለዚህ ጉዳይ ከ የኔዘርላንድ ኤምባሲዎች ጋር ኣብሮ ይሰራል። በደብዳቤው ውስጥ የቤተሰቦቻችሁ አባላት እና እርስዎ ምን ማድረግ እንዳለባችሁ ይናገራል።

በመጀመሪያ, ቤተሰቦችዎ በአቅራቢያቸው ከሚገኘው የ ኔዘርላንድ ኤምባሲ ቀጠሮ ይይዛሉ። በቀጦሮው ቀን ደግሞ ወደ ኤምባሲው ሕንጻ ይሄዳሉ። ዶክተር, ነርስ ወይም ሌላ ሰው ከቤተሰብዎ አባላት ጉንጭ ውስጥ ምራቅ ይወስዳል።. ይሄ የሚደረገው ለዛ ብሎ በተሰራው ልዩ ኣንጨት ነው። ከጉንጭ ምራቅ መውሰድ ምንም አይጎዳም። ለጤንነት ደግማ ጎጂ ኣይደለም። የ DNA ምርመራው ወደ ኔዘርላንድ ወደ IND ይላካል። የቤተሰብዎ አባላት በኤምባሲው ውስጥ ዲ ኤን ኤ (DNA) ምርመራ ከሰጡ ቦኋላ ወዲያውኑ ለእርስዋ ማሳወቅ አለባቸው። በቀጣዩ ቀን ኡትረኽት በሚገኘው ቢሮ ውስጥ የዲ ኤን ኤ (DNA) ምርመራ ለመስጠት ወደ www.ind.nl የሚል የ ኢንተርነት ድህረ-ገጽ በመግባት ቀጠሮ መያዝ ይችላሉ። ያንን ለራስዎ ያደርጉታል። እንዲሁም ደግሞ አስፈላጊ ከሆነ በኔዘርላንድስ ለሚገኙ ለቤተሰብዎ አባላት ጭምርም ያደርጋሉ።

IND ከጉንጭዎ የወሰደው ምራቅ እና ከቤተሰብዎ አባላት ጉንጭ የወሰደውን ምራቅ ይመረምራል። የ DNA ምርመራ ውጤቱ እስኪታወቅ ጥቂት ወራት ሊወስድ ይችላል። ውጤቱ ከታወቀ ደግሞ ከ IND መረጃ ያገኛሉ።

> የቤተሰብዎ አባላት ለተጨማሪ ምርመራ ወደ በአቅራቢያቸው ከሚገኘው የ ኔዘርላንድ ኤምባሲ ይሄዳሉ። እንዲሁም ደግሞ mvv ለመውሰድ ለሚደረገው ሂደት ለማካሄድ ወደ በአቅራቢያቸው ከሚገኘው የ ኔዘርላንድ ኤምባሲ ይሄዳሉ። አንዳንድ ጊዜ የቤተሰብዎ አባላት ወደ ኔዘርላንድ ኤምባሲ ለመሄድ ድንበር ተሻግረው ወደ ሌላ ኣገር መሄድ ኣለባቸው። ይህ ወደ ትውልድ አገራቸው ተመልሶ ለመግባት ችግር የሚፈጥርላቸው ሊሆን ይችላል። የዚህ ጉዳይ ሃላፊነት ሙሉ በሙሉ የቤተሰብዎ አባላት ነው። ድንበሮችን ለመሻገር ስለሚቻልበት ሁኔታ በአስቸኳይ የቤተሰብ አባላትዎን ያማክሩ። እንዲሁም የኔዘርላንድ ኤምባሲ በሚገኝበት አገር ለመግቢያ, ለመቆየትና ለመውጣት የሚመለከታቸውን ደንቦች እና ህጎች በተመለከተ ከ የቤተሰብዎ አባላት ጋር መመካከር ኣለባቹሁ። ከ ኔዘርላንድ ኤምባሲ ጋር ቆጦሮ ከመያዝዎ በፊት እነዚህን ጉዳዮች ማመቻቸት ኣለባቹ።

## 5ኛ ደረጃ፥ ቃለ-ምልልስ በኤምባሲ

የ DNA ምርመራ ላማካሄድ የማይቻል ከሆነ ወይም IND የ DNA ምርመራ ከተደረገ ቦኋላ ኣንዳንድ ጥያቄዎች ካሉት ከዚያ IND የቤተሰብዎ አባላት ለቃለ መጠይቅ ሊጋብዟቸው ይችላሉ። ቃለ-መጠይቁ የሚደረገው በውጭ አገር በ የኔዘርላንድ ኤምባሲ ነው። በቃለ መጠይቁ ውስጥ የቤተሰብ አባሎችዎ ማን እንደሆኑ እና ከእርስዎ ጋር ያላቸው ግንኙነት ምን እንደሆነ ማስረዳት ይችላሉ። IND ለእርስዎም እዚህ በኔዘርላንድ ለቃለ መጠይቅ ሊጋብዝዎት ይችላል። በኤምባሲው ቃለ መጠይቅ እስከሚያዘጋጅ ድረስ በርካታ ወራት ሊወስድ ይችላል።

## 6ኛ ደረጃ፥ ውሳኔ

IND የሁሉም ምርመራዎች ውጤት እስከሚታወቅ ድረስ ይጠባበቃል። ከዚያ የቤተሰብዎ አባላት ሁሉንም ሁኔታዎች ያሟሉ እንደሆነ ያረጋግጣል። እርስዎ ደግሞ ለቤተሰብዎ አባላት ያቀረቡት ማመልከቻዎ ላይ ውሳኔ ያገኛሉ። ይህም በሕጉ መሠረት ማመልከቻው ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ በሶስት እስከ ስድስት ወራት ውስጥ መደረግ አለበት። ስራ በሚበዛበት ወቅት ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ ብዙ ጊዜ ይወስዳል።

- አዎንታዊ ውሳኔ፥ የቤተሰብዎ አባላት ሁሉንም ሁኔታዎች ካሚሉ, IND ማመልከቻዎችን ያፀድቃሉ። ኢንደዚሁም IND ውሳኔውን ለእርስዎ እና ለኔዘርላንድ ኤምባሲ ይልካል። እርስዎ ደግሞ ስለ IND ውሳኔዎ ለቤተሰብዎ አባላት ያሳውቃሉ።
- ኣሉታዊ ውሳኔ፥ የቤተሰብዎ አባላት ሁሉንም ቅድመ ሁኔታዎች ያላሟሉ ከሆነ, IND ማመልከቻውን ውድቅ ያደረጋል። የቤተሰብዎ አባላት ይህንን ውሳኔ በእርስዎ በኩል ኣድርገው ሊቃወሙት ይችላሉ። እርሰዎ ወይም የ VWN ተባባሪዎ በዚህ ረገድ ሊረዳዎ የሚችል ጠበቃ መፈለግ ትችላላቹሁ።

## 7ኛ ደረጃ፥ ከአዎንታዊ ውሳኔ በኋላ mvv እንዲሰጣቹ ማመቻቸት

### ቀጠሮ

የቤተሰብዎ አባላት ይህ mvv አወንታዊውን ውሳኔ በተላለፈበት በ 3 ወራት ውስጥ መውሰድ ኣለባቸው። ይህን ለማድረግ ደግሞ ከኔዘርላንድ ኤምባሲ ጋር ቀጠሮ መያዝ አለባቸው። ይህ ኤምባሲ ደግማ በማመልከቻ ቅጹ ላይ የተሞላ ኤምባሲ መሆን ኣለበት። ወይም ደግሞ ቀደም ብለው የቤተሰብዎ አባላት ለተጨማሪ ምርምር ብለው የሄዱት ኤምባሲ መሆን ኣለበት።

### ኤምባሲ፥ የ mvv ፎርም, የጣት አሻራዎች, ፊርማ እና ፓስፖርት ማቅረብ

የቤተሰብዎ አባላት የራሳቸውን የፓስፖርት ፎቶግራፍ ይዘው መምጣት አለባቸው። የፓስፖርት ፎቶ የተወሰኑ መስፈርቶችን ማሟላት አለበት። mvv ለማመቻቸት፣ የቤተሰብዎ አባላት በመጀመሪያ በኤምባሲው ላይ የ mvv መስጫ ቅጽ ይሙሉ። ከዚያ በኋላ አንድ ሠራተኛ ከቤተሰብዎ አባላት የጣት አሻራዎችን ይወስዳል። የቤተሰብ አባሎችዎም ፊርማቸውን ያሰፍራሉ። የከኔዘርላንድ ኤምባሲ የቤተሰብዎን ፓስፖርት ይወስዳሉ። ይህ የሚያስፈልገው ደግሞ mvv ለመስጠት ነው። በዚያን ጊዜ የ ፓስፖርቱ የኣገልግሎቱን ቀነ ገደብ ገና 6 ወር ወይም ከዚያ በላይ የቀረበት መሆን አለበት። የእርስዎ ቤተሰብ አባላት ፓስፖርት የለባቸውም? እንደዛ ከሆነ ብዙውን ጊዜ ጊዝያዊ የኔዘርላንድ ፓስፖርት (LP) ማግኘት ይችላሉ። LP ለአንድ ነጠላ ጉዞ ብቻ ሊያገለግል የሚችል የጉዞ ሰነድ ነው። ለዚህ የሚሆን እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል 2 ተጨማሪ የፓስፖርት ፎቶ መስጠት አለበት። የእርስዎ ቤተሰብ አባላት LP ማግኘት ካለባቸው IND ለ ኤምባሲ ያሳውቃል።

### mvv መስራት እና በፓስፖርት ውስጥ ማስፈር

ኤምባሲው mvv ይሰራል። ይህ ቢበዛ ቢበዛ 2 ሳምንታት ይወስዳል። ሁሉም ነገር ዝግጁ ሲሆን mvv (ተለጣፊ) በፓስፖርት ይለጠፋል። ኤምባሲው የቤተሰብዎን አባላት ፓስፖርቶን እና mvv እንዲወስዱ ይጋብዛል።

### ኤምባሲ፥ mvv እና መረጃን መቀበል

የቤተሰብዎ አባላት ወደ ኤምባሲው ይመለሳሉ። የቤተሰብዎ አባላት mvv የተለጠፈበት ፓስፖርታቸውን ይቀበላሉ። ወይም ደግሞ mvv የተለጠፈበት ጊዝያዊ የኔዘርላንድ ፓስፖርት (LP) ይቀበላሉ። በተጨማሪም ወደ ኔዘርላንድ ከገቡ በኋላ ምን ማድረግ እንዳለባቸው በጽሁፍ መረጃ ይቀበላሉ።

> ለ የቤተሰብ አባሎችዎ LP መስጠት የሚችሉ ከ የትውልድ ሀገርዎ ውጭ የሚገኙ የኔዘርላንድ ኤምባሲዎች ብቻ ናቸው።

### 8ኛ ደረጃ፥ ጉዞ ወደ ኔዘርላንድ

የቤተሰብዎ አባላት mvv ከተቀበሉ ቦኋላ ወደ ኔዘርላንድ ሊጓዙ ይችላሉ። አንዳንድ ጊዜ በውጭ አገር ለሚገኙ ለቤተሰብ አባሎችዎ የሚያገለለግሉ ልዩ የሆኑ የመውጣት ደንቦች አሉ። የስደተኞች ተባባሪዎች ይህንን ለማካሄድ ሊረዳችሁ ይችላሉ። mvv ለ 90 ቀናት ልያገለግል ይችላል። ለስንት ቀናት ማገልገል እንደሚችል እዛ ተለጣፊ mvv ስቲከር ላይ ተጽፎ ይገኛል። በዚህ ላይ ሁለት ቀናት አሉ።

- የሚጀምርበት ቀን (ከዚህ ቀን ጀምሮ mvv ኣገልግሎት መስጠት ይጀምራል)
- የሚጨርስበት ቀን (ከዚህ ቀን ቦኋላ mvv ኣገልግሎት መስጠት ያበቃል)

የቤተሰብዎ አባላት ወደ ኔዘርላንድ ለመጓዝ ራሳቸው የአውሮፐላን ትኬት መግዛት አለባቸው። IND የሚሰጡት ምክር፣ የአውሮፐላን ትኬት መግዛት ያለበት mvv ከተቀበሉ በኋላ ነው። VWN ያግዝዎታል? አንዳንዴ የጉዞ ወጪዎች በከፊል ሊከፈልሎት ይችላል። ያሉት ኣማራጮች እና እድሎች ምን እንደሆኑ ለማወቅ ለርስዎ የ VWN ተባባሪዎ ይጠይቁ።

## ክፍል 2 - ለቤተሰብዎ አባላት የኔዘርላንድ የጥገኝነት አሰራር ሂደት በ 2 ደረጃዎች

### 1ኛ ደረጃ፥ እዚህ ከገቡ ቦኋላ ቴሌፎን በመደወል ማሳወቅ

የቤተሰብ አባላትዎ በ 90 ቀናት ውስጥ ወደ ኔዘርላንድ መጓዝ እና ከገቡ በኋላ ደግሞ መግባታቸውን ስልክ በመደወል ማሳወቅ አለባቸው። የቤተሰቦቻችሁ አባላት ወደ ኔዘርላንድ በገቡበት ቀን፣ የቤተሰብ አባላትዎ ወይም እርስዎ ወደ የ IND የቆይተው ተጓዦች የቀጠሮ መስመር (Afsprakenlijn Nareizigers) መደወል ኣለብዎት። በዚህ መንገድ ደግሞ mvv ኣገልግሎቱን ኣሁንም ገና እንዳለ ለማረጋገጥ ይቻላል። የቆይተው ተጓዦች የቀጠሮ መስመር (Afsprakenlijn Nareizigers) የቴሌኮሙኒኬሽን የስልክ ቁጥር እዛ የአዎንታዊ ውሳኔ የተላከበት በደብዳቤ ውስጥ ይገኛል።

የቆይተው ተጓዦች የቀጠሮ መስመር (Afsprakenlijn Nareizigers) ሰራተኛ ለቤተሰብዎ አባላት መቸ እና ወደ የትኛው የመጠለያ ማዕከል (COA) ሂደው ማመልከት እንዳለባቸው ያሳውቃል። COA መጠለያ ያዘጋጃል እንዲሁም ደግሞ በሂደቱ ውስጥ ድጋፍን ያመቻቻል። IND እና VWN በመጠለያው ቦታም ይገኛሉ።

### 2ኛ ደረጃ፥ የጥገኝነት ሂደት እና ለቤተሰብዎ አባል ፈቃድ

በቀጠሮው ቀን ቤተሰቦችዎ ወደ መጠለያ ቦታ ይሄዳሉ። የጥገኝነት ማመሌከቻዎቻቸው ሂደት ቢያንስ 4 ቀናትና 3 ለሊቶች ይወስዳል። የቤተሰብዎ አባላት በመጠለያው ቦታ ይተኛሉ። እርስዎ ደግሞ ቤትዎ ውስጥ ይተኛሉ።

> በአብዛኛው ሂደቱ 4 ቀናትን ይወስዳል። አንዳንድ ጊዜ ጥርጣሬዎች ወይም ግልጽ ያልሆኑ ነገሮች ይገኛሉ። እንደዚህ ከሆነ IND የቤተሰብዎ አባላት ወደ አጠቃላይ

ለየቤተሰብዎ አባላት ሂደቱን በሚካሄድበት ግዜ በመጠለያው ቦታ እነኚህ ነገሮችን ይፈጸማሉ፥

- የ IND ሠራተኛ ማንነታቸውን እና የጣት አሻራቸውን ይመረምራል ያጣራል። IND ዲጂታል የፊት ፎቶን ይወስዳል እንዲሁም የጣት አሻራዎችን ግልጽ ካልሆነ ወይም የሌለ ከሆነ የጣት አሻራዎችን ይወስዳል።
- የቤተሰብዎ አባላት የቲቢ ምርመራ ያደርጋሉ። ይህ የሚወሰነው በ የቤተሰብዎ አባላት የመጡበት አገር ነው።
- የቤተሰብዎ አባላት በ VWN ስለ ሂደቱ ማብራርያ ይሰጥባቸዋል።
- የቤተሰብዎ አባላት ከ IND ጋር አጭር ንግግር አላቸው። IND ለቤተሰብዎ አባላት ውሳኔ ይሰጣል። ይህ ደግሞ በሌላ ሰው የጥገኝነት ፍቃድ ላይ የተመሠረተ የጥገኝነት ፍቃድ ማግኘታቸው የሚያሳይ ደብዳቤ ነው። እና IND ለቤተሰቦችዎ የመኖሪያ ፍቃድዎን ይሰጣቸዋል። ይህ የማይቻል ከሆነ IND ስለ ቀጣይ የሂደቱን አሰራር ይበልጥ ያብራራል።
- የቤተሰብዎ አባላት ከ COA የሥራ ባልደረባ ጋርም አጭር ውይይት አላቸው።
- በተጨማሪም የቤተሰብዎ አባላት ለማዘጋጃ ቤት ሠራተኛ ያነጋግራሉ። ማዘጋጃ ቤት የቤተሰብዎ አባላት ዝርዝር መረጃ በ የህዝብ መዝገብ ላይ ይመዘግባል።
- በመጨረሻው ቀን የቤተሰብዎ አባላት ከመጠለያው ቦታ ይወጣሉ። ወደ ቤትዎ ይሄዳሉ። ይህ ካልሆነ ግን COA እና ማዘጋጃቤት በመተባበር ለእነሱ የሚሆን መጠለያ ያዘጋጃሉ።

## ራሱን የቻለ የግል የጥገኝነት ማመልከቻ ማስገባት

በኔዘርላንድስ ውስጥ የቤተሰብዎ አባል በርስዎ የጥገኝነት ፍቃድ ላይ የተመሠረተ ፍቃድ ይቀበላሉ። ይህ በርስዎ የጥገኝነት ፍቃድ ላይ የተመሠረተ ጊዜያዊ ፈቃድ ነው። IND የእርስዎ የጥገኝነት ፈቃዶዎን ከነጠቀ ወይም ካላስረዘመው ከዚያ IND የቤተሰብዎ አባል የጥገኝነት ፈቃድም መንጠቅ ይችላል ማለት ነው። ወይም ራሱን የቻለ የግላቸውን የጥገኝነት ፍቃድ ማግኘት ይችሉ እንደሆነ ይገመግማል። የቤተሰብዎ አባል ከእርስዎ ጋር ያላቸው የቤተሰብ ትስስር እና ቁርኝት የቆመ እንደሆነ IND የቤተሰብዎ አባል የጥገኝነት ፍቃድ መንጠቅ ይችላል። ይህ የሚሆነው የቤተሰብዎ አባላት ከአሁን በኋላ ከእርስዎ ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት እና ዝምድና የሌላቸው ከሆነ ነው። ወይም የቤተሰብ አባልዎ ገና ልጅ ሆኖ በኣንድ አመት ውስጥ እራሱን ችሎ ተለይቶ የሚኖር ከሆነ ነው።

የቤተሰብዎ አባል ራሱን የቻለ የግላቸው የጥገኝነት ማመልከቻ ማቅረብ ይፈልጋሉ? እንደዝያ ከሆነ በመጠለያው ውስጥ ከ IND ጋር በሚያደርጉት ቃለ-መጠይቅ ይህንን ሊያመለክቱ ይችላሉ። የ IND ሰራተኛው ስለዚህ ማብራሪያ ይሰጣል። የቤተሰብዎ አባል ራሱን የቻለ የግላቸው የጥገኝነት ማመልከቻ ካቀረቡ አጠቃላይ የሆነ የጥገኝነት አሰራር ነው የሚከተሉት። አጠቃላይ የጥገኝነት ሂደቱ ረዘም ያለ ጊዜ ይወስዳል። ከዚያም ደግም IND የቤተሰብ አባሎቻችሁ ከ የኔዘርላንድ መንግስት ጥበቃ እንዲደረግላቸው ያስፈልግ እንደሆነ ይመረምራል። እንደዚያ ከሆነ ለተወሰነ ጊዜ ራሱን የቻለ የግል የጥገኝነት ፈቃድ ይሰጣቸዋል። የቤተሰብዎ አባላት ይህ ራሱን የቻለ የግል የጥገኝነት ማመልከቻ ቀስ ብለው በኋላ ማመልከት ይችላሉ።

> የቤተሰብ አባልዎ የቤተሰብዎ አካል ከሆኑ ቤተሰብን መልሶ ማገናኘት ሲባል ወደ ኔዘርላንድስ መጓዝ ይችላሉ። አንድ ሰው ከ (ጋብቻ) ባለቤት እና ከወለዳቸው (ባዮሎጂካዊ) ልጆች ጋር ቤተሰባዊ ግንኙነት ሊኖረው ይችላል። አንድ ልጅ ከሁለቱም ወላጆቻቸው ጋር ቤተሰባዊ ግንኙነት ሊኖረው ይችላል። አብዛኛውን ጊዜ አንድ የቤተሰብ አባል የአንድ ቤተሰብ ኣካል ብቻ ነው መሆን የሚችለው። ለምሳሌ, አንድ ወጣት ሰው ከወላጆቹ ጋር የቤተሰብ ኣካል ሆኖ እንዲሁም እንደገና ከ (ጋብቻ) ባለቤቱ የራሱ ቤተሰብ ኣካል ሊሆን አይችልም። በእነዚህ እና በሌሎች ሁኔታዎች ቤተሰቡን መልሶ ለመገናኘት ወደ ኔዘርላንድ የተጓዘ የቤተሰብ አባልዎ ለሌሎቹ የቤተሰብ አባላት ወደዚህ እንዲመጡ ጋባዥ (ስፖንሰር) ሊሆን አይችልም። እንዲሁም እሱ ራሱ የቻለ የጥገኝነት ፍቃድ ያለው ከሆነ ደግሞ ጋባዥ (ስፖንሰር) ሊሆን አይችልም።

## ማመልከቻውን መሰረዝ

የቤተሰብ አባሎችዎ በማንኛውም ጊዜ ማመልከቻውን መሰረዝ ይችላሉ። በዚህ ሁኔታ የበለጠ በ የ VWN ተባባሪዎ በኩል መደረግ ኣለበት። ወይም ይህንን በቀጥታ ወደ IND ማመልከት ኣለባቹሁ። የቤተሰብዎ አባላት ማመልከቻውን ከሰረዙ እና በኋላ ላይ እንደገና መልሰው ለየቤተሰብ መልሶ ማገናኘት ሂደት ማመልከቻ ያቀረቡ እንደሆነ በአብዛኛውን ግዜ ሁሉም ቅድመ ሁኔታዎችን አያሟሉም ተብለው ይወሰንባቸዋል።

## የእርስዎ የግል መረጃ ኣጠቃቀም

የግል መረጃ ስንል  ሁሉም አይነት መረጃዎች ስለእርስዎ ማለት ነው። ከዚህ ጽሁፍ ጋር ትብብር ያላቸው ድርጅቶች ከታች ተዘርዝረው ይገኛሉ። እነዚህ ድርጅቶች የማመልከቻዎ ጉዳይ በሚያዩበት ግዜ፣ የሆነ ጥያቄ ብምታቀርቡበት ግዜ ወይም የሆነ ነገር ለማሳወቅ ብትፈልጉ እነኝህ የግል መረጃዎን ይጠቀማሉ።. አስፈላጊ ከሆነ ደግሞ የሚፈልጉትን መረጃዎን ለእርስዎ ይጠይቃሉ ወይም ከሌሎች ድርጅቶች እና ግለሰቦች ይጠይቁታል። እነዚህ ድርጅቶች የእርስዎ መረጃዎን ይጠቀማሉ እና ያከማቻሉ እንዲሁም ደግሞ በህግ የግድ ሲሆን የእርስዎ የግል መረጃ ወደ ሌሎች ድርጅቶች ያስተላልፋሉ። በ የግላዊነት ህጎች ውስጥ የእርስዎ መረጃዎን የሚጠቀሙ ድርጅቶች ያለባቸው ግዴታዎች ተጽፈው ይገኛሉ። ለምሳሌ, የእርስዎን መረጃ በጥንቃቄ እና ዋስትና ባለበት ሁኔታ መያዝ አለባቸው። የግላዊነት ህጎችም መብቶችዎን ያካትታሉ, ለምሳሌ:

- በድርጅቶች የተያዙ የእርስዎ መረጃዎን ማየት፡
- ድርጅቶች የእርስዎ መረጃዎን ምን እንደሚያደርጓቸውና ማወቅ እና ለምን?
- የእርስዎ መረጃዎን ወደ የትኛው ድርጅት እንደተላለፉ ማወቅ፡

ስለ እርስዎ የግል መረጃ እና መብትዎ ሂደት የበለጠ ማወቅ ይፈልጋሉ? ስለዚህ የድርጅቶችን የኢንተርነት ድህረ-ገጽ ይመልከቱ። በዚህ በራሪ ጽሁፍ የታችኛው ክፍል የኢንተርነት ድህረ-ገጾች ማግኘት ይችላሉ።

## ተደጋግመው የሚጠየቁ ጥያቄዎች

### የቤተሰብዎ አባላት ከጠፉ ለ mvv-nareizigers asiel ማመልከቻ ማቅረብ ይችላሉ?

አዎን። ከቤተሰብዎ አባላት ጋር ያለዎትን ግንኙነት ከጠፉ፣ ማመልከቻ ማስገባት ይችላሉ። ምክንያቱም ደግሞ ማመልከቻ በማቅረብ ብቻ ነው የድህረ ጉዞ ቀነ ገደቡን ኣስተማማኝ ማድረግ የምትችሉት። በአንዳንድ ሁኔታዎች ቀይ መስቀል የቤተሰብዎን አባላት ለማግኘት ይረዳዎታል። ይህ ተከታትሎ መድረስ ተብሎ ይጠራል። የ VWN ተባባሪዎ በዚህ በኩል ሊተባበርዎት ይችላል።

### ቤተሰቦቹ በኔዘርላንድ ኤምባሲ ውስጥ ወንጀለኛ አለመሆናቸውን የሚገልጽ የምስክር ወረቀት (antecedentenverklaring) እንዲፈርሙ ማድረግ ይቻላል?

አይ, ይህ የማይቻል ነው። የተፈረመባቸውን (antecedentenverklaring ) ወደ ኔዘርላንድ መላክ ላይ ችግሮች አሉ? ከ IND ጋር ምን የተሻለ ነገር ሊደረግ እንደሚቻል ተመካከሩ።

### አሁንም ገና በ COA መጠለያ ቦታ ላይ ከሆንክ ከቤተሰብህ አባላት ጋር የምትኖረው የት ነው?

ማዘጋጃ ቤቱ እና COA በዚህ ላይ በጋራ ይሰራሉ። ለ COA ተባባሪዎ ያሉትን ኣማራጮች ይጠይቁ።

### ይህን ጽሑፍ ካነበቡ በኋላ አሁንም ጥያቄዎች አሉዎት?

እነዚህን ጥያቄዎች ለ የ VWN ተባባሪዎ ሊጠይቋቸው ይችላሉ።

### ቅሬታ አለዎት?

በቤተሰብ መልሶ ማገናኘት ሂደት ውስጥ የሚሳተፉ ሁሉም ድርጅቶች በሙያዊ ብቃት እና በጥንቃቄ ሥራቸውን ያከናውናሉ።
በአንዳንድ ድርጅቶች ውስጥ ለቤተሰብ አባላትዎ ኣያያዝ በሚመለከት ቅራኔ ኣላቸው? እንደዛ ከሆነ ኣቤቱታ ማቅረብ ይችላሉ። የ VWN ተባባሪዎ በዚህ በኩል ሊተባበርዎት ይችላል።

**ይህ እትም የነዚህ ድርጅቶች የጋራ መግለጫዎች ናቸው፥**

ለጥገኝነት ፈላጊዎች ማዕከላዊ ኤጀንሲ | www.coa.nl
የ መመለስና የመነሻ አገልግሎት | www.dienstterugkeerenvertrek.nl
የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት | www.ind.nl
የሕግ እርዳታ ምክር ቤት | www.rvr.org
የስደተኞች ተባባሪ ድርጅት ኔዘርላንድ | www.vluchtelingenwerk.nl

**Iይህን ስራ የመደበው፥**

ይህ በራሪ ወረቀት የተዘጋጀው በፍትህ እና ደህንነት እና ፍትህ ሚኒስቴር የስደተኞች ፖሊሲ ዳይሬክቶሬት በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ነው
www.rijksoverheid.nl

በዚህ ህትመት ይዘታ ማንኛውንም መብቶች ማግኘት አይችሉም።
ትርጉሙ የትርጓሜ ልይነቶችን የሚያመጣ ከሆነ በኔዘርላንደኛ ቋንቋ የቀረበው ጽሁፍ መሪ ይሆናል።